# Learning by Ear 2013

"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" – "መዘዙን መቀበል"

EPISODE 26: አዲስ ጅማሬ

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ምህረት GIVES BIRTH**

- ምህረት (F, 15)
- ዶ/ር ሮቤል (M, LATE 40s)

**SCENE 2: DOCTOR TALKS TO ወ/ሮሉሊት**

- ወ/ሮሉሊት (F, 40)
- ዶ/ር ሮቤል (M, LATE 40s)

**SCENE 3: STUDENTS VISIT ምህረት IN HOSPITAL**

- ትዕግስት (F, 15)
- አልማዝ (F, 16)
- ምህረት (F, 15)
- ንጉሴ (M, 16)

**SCENE 4: ንጉሴ WINS SWIMMING COMPETITION**

- COMMENTATOR (M/F, AGE UNIMPORTANT)
- አልማዝ (F, 16)
- ትዕግስት (F, 15)
- ንጉሴ (M, 16)

- **PRINCIPAL JULIETTE (F, 50)**
- **CROWD (MAINLY STUDENTS, M/F, 10 - 12 PEOPLE)**

**INTRO**

**1. NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤  ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ  ስለ አፍሪቃውያን ታዳጊ ወጣቶች  የሚተርከዉና ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ነዉ።  ዛሬ "መዘዙን መቀበል" በተሰኘዉ ሁለተኛ ዙር ድራማ   ሃያ ስድስተኛውና የመጨረሻ ክፍል ላይ ደርሰናል። ታድያ የመጨረሻዉን ክፍል ከመጀመራችን በፊት በቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ታዳጊ ልጆች ላይ እስከ አሁን ምን እንደተከናወነ መለስ ብለን እንቃኝ። መጀመሪያ አካባቢ ትንሽ ችግር ከተፈጠረ በኋላ ከላቦሪያ የመጣችው የዝውውር ተማሪ አልማዝ ከምህረት እና ትዕግስት ጋር ጓደኛ ሆናለች። የክፍል ጓደኛቸው ንጉሴም በእጽ የተነሳ ከቤተሰቡ ጋር የነበረበትን ችግር አስተካክሏል። ግን ለምህረት የሚሰማው  ስሜት አልለቀቀውም፤

***KW BEGIN***

**2. EPISODE 16, LINES 33 – 35:**

*ንጉሴ:* ምህረት፣ ናፍቀሽኛል።.

*ምህረት:*  ንጉሴ፣ እኔ...እያስጨነቅሽኝ ነው።

*ንጉሴ:*  ይቅርታ። (...) ግን ለአንቺ ግልጽ ሆኜ ያለኝን ስሜት መንገር እንዳለብኝ ይሰማኛል።

***KW END***

**3. NARRATOR:**

ባለፈው  ክፍል ድራማ ምህረትን አሟት ነበር። እናቷን ድንገት እንዲያ ስታስደነግጣት እቤት ውስጥ እያገዘቻት ነበር።:

**4. EPISODE 25, LINES 97, 117 - 118:**

<u>ወ/ሮ ሉሊት</u>*:* ምህረት ነይ! አንቺ የስምንት ወር ነፍጡር ነሽ። አሁንም ልታግዢኝ ትችያለሽ! (…)

***SFX (117): THUD AS ምህረት FALLS DOWN***

<u>ወ/ሮ ሉሊት</u> ***(118):*** ምህረት! ምህረት፣ ደህና ነሽ? ***(slaps her cheeks)***

**5. NARRATOR:**

ወ/ሮ ሉሊት ሴት ልጃቸውን ወደ ሐኪም ቤት አምጥተው ለሁለት ቀናት እዚያው ነበሩ። እናስ ተሻላት? መልሱን ልናገኝ ነው… ይህ የመጨረሻ ክፍል ጭውውት“አዲስ ጅማሬ” ይሰኛል

**<u>SCENE 1: ምህረት GIVES BIRTH</u>**

**6. ATMO: HOSPITAL ATMO**

**7. ምህረት:** **(pants and screams)** አይይይይ! ሞትኩ እኮ!

**8. ዶ/ር ሮቤል:** **(gently)** በርትተሻል፣ ምህረት። ልጅሽ መምጣት የነበረበት በቀጣዮቹ አራት ሳምንታት ውስጥ እንደነበረ አውቃለሁ፤ ግን ከዚያ ይልቅ አሁን ካልወጣሁ ብሏል። እናም ርዳታሽን ይፈልጋል።.

**9. ምህረት:** **(exhausted)** እሺ

**10. ዶ/ር ሮቤል:** መተንፈስ እንዳትረሺ! አሁን ወደ ውስጥ አየር ሳቢ! ከዚያም አስወጪ!

**11. ምህረት:** **(breathes heavily in and out)**

**12. ዶ/ር ሮቤል:** እና አሁን፣ ግፊ!

***KW BEGIN***

**13.** ምህረት: **(screams)** አልቻልኩም፣ ዶክተር፣ ባክህን፣ አልቻልኩም!

**14.** ዶ/ር ሮቤል: ትችያለሽ፤ ጠንካራ ወጣት ሴት ነሽ፣ ምህረት። ከአንቺ በፊት ብዙ ሴቶች ችለውታል። አሁን ግፊ-በቅድመ ወሊድ ክትትል ጊዜሽ የትምህርት ቤትሽ ነርስ እንዳሳየችሽ፣ አስታወስሽ? ግፊ!

**15.** ምህረት: **(screams, pants)**

**16.** ዶ/ር ሮቤል: **(to himself)** ህምም… ጨቅላው ተንጋሎ የመጣ ይመስላል።.

**17.** ምህረት **(still panting)** ምን ማለት ነው ዶክተር? ልጁ ደህና ነው?

**18.** ዶ/ር ሮቤል: **(reassuring)** ልጁ ደህና ነው፣ ምህረት። እንደምታውቂው ህፃን ሲወለድ ጭንቅላቱን ማስቀደም አለበት። ብዙውን ጊዜ ልጆች ፊታቸውንወደ ታች አዘቅዝቀው ነውየሚወለዱት። አሁን ግን ጨቅላው ጭንቅላቱን ቢያስቀድምም ፊቱን ግን ወደ ላይ አድርጎ ተንጋሎ እየመጣ ነው ማለት ነው። ይህ ሁኔታ የውልጃ ሂደቱን ለአንቺም ለልጁም ከባድ ያደርገዋል። ሆኖም ትልቅ ችግር አይደለም። አሁንም ልጅሽ ከተንጋለለበት ሊዞር ይችላል።.

***KW END***

**19.** ምህረት: **(pants)**

**20.** ዶ/ር ሮቤል: በርቺ፣ ምህረት፣ ትችያለሽ። ግፊ!

**21. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: DOCTOR TALKS TO ወ/ሮሉሊት**

**22. ATMO: HOSPITAL WAITING ROOM**

**23. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**24. SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS ወ/ሮሉሊት GETS UP**

**25.** ወ/ሮሉሊት: **(panicking)** እንዴት ነው፣ ዶክተር ሮቤል? ልጄ ምህረት እንዴት ናት? ላያት ፈልጌ ነበር፣ ልገባ ግን አልፈቀዱልኝም!

**26.** ዶ/ር ሮቤል: የምህረት እናት ልጅዎ ደህና ናት፡፡ ባለፈው ጊዜ ከሄዱ ጀምሮ ምጥ ይዟታል እና ትንሽ ስለተቸገረች በሀኪም እርዳታ መውጣት ነበረበት፡፡ ቢሆንም ጥሩ ዜና አለኝ፡፡ ልጅዎ ምህረት ሴት ልጅ ተገላግላለች። ሴት የልጅ ልጅ አግኝተዋል፡፡

**27.** ወ/ሮሉሊት: **(excited)** ምን? ደህና ናት? ምህረቴ? ማለቴ …ህጻኗ…? ማለቴ ሁለቱም!

**28.** ዶ/ር ሮቤል: ሁለቱም ደህና ናቸው፡፡

**29.** ወ/ሮሉሊት: ግን አልገባኝም… ገና የስምንት ወር ነፍሰጡር ነበረች! ህጻኗ ምን አጣድፏት ነው?

**30.** ዶ/ር ሮቤል: በአጠቃላይ ለመናገር፣ ብዙ ጊዜ ጊዜው ሳይደርስ የመውለድ ስጋት ያለባቸው ትልልቆች ናቸው፡፡ ምህረትም በጣም ቀጭን ስትሆን ትንሽ ህመም ነበራት፡፡ ባለፈው እራሷን የሳተችው ለዚህ ነው፡፡ እና ህመሙ ስለነበረባት የእንሽርት ውሃው ፈሰሰና የምጥ ህመም ጀመራት፡፡.

**31.** ወ/ሮሉሊት: ወይኔ ልጄን!

**32.** ዶ/ር ሮቤል: አይጨነቁ-በጣም ይሻላታል። ለማንኛውም እንደታመመች ወዲያውኑ ምህረትን እዚህ ማምጣትዎ ጠቅሟታል። ያን በማድረጎ ያላቋረጠ የህክምና ክትትል አድርገንላታል፤ የሚያስፈልጋትን እርዳታ በሙሉም ሰጥተናታል። አፍሪቃ ውስጥ ብዙዎቹ ሊወልዱ የተቃረቡ እናቶች ይህንን አያገኙም።.

**33.** ወ/ሮሉሊት: አሁን ያሉት የት ነው? ላያቸው እችላለሁ?

**34.** ዶ/ር ሮቤል: ምህረት ክፍል ሰባት ውስጥ ብትሆንም ህጻንዋን ግን በመንከባከቢያ ክፍል ውስጥ ነች። እርሷን በኋላ ያይዋታል። አሁን ምህረት ጋር ልውሰድዎት።

**35. SFX: FOOTSTEPS, TWO PEOPLE**

**36. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 3: STUDENTS VISIT ምህረት IN HOSPITAL

**37. SFX: BABY CRYING**

**38.** አልማዝ: እሽ! አታልቅሽ! አክስትሽ አልማዝ ይህቹትልሽ... **(laughs and speaks baby language)** እሽሹ እሽሹ እሽሹ...

**39. SFX: BABY STOPS CRYING**

**40.** ትዕግስት: ምህረት፣ ጓደኛችን አልማዝ ምትሀታዊ ሀይል ያላት ትመስላለች!

**41. GIRLS:** **(laugh)**

**42.** ምህረት: ትዕግስት-አልማዝ-ስላየኋችሁ ደስ ብሎኛል!

**43.** ትዕግስት/አልማዝ: እኛም ምህረት.

**44.** ትዕግስት: ትንሿ ልጅሽ ስታምር! **(puzzled)** ግን በጣም ትንሽ ናት! እዚህ ነገር ውስጥ ለምን አስገቧት?

**45.** አልማዝ: ያ እኮ መንከባከቢያ ነው፣ ትዕግስት። ጊዜያቸው ሳይደርስ የተወለዱ ልጆችን እዛ ውስጥ ሲያስቀምጧቸው ሙቀትም ጥንቃቄም ስለሚያገኙ በደንብ ያድጋሉ።

***KW BEGIN***

**46.** ትዕግስት: ልይዛት እችላለሁ፣ በእናታችሁ?

**47.** ምህረት: አትችይም፣ ትዕግስት፣ ዶክተሩ ምንም አይነት በሽታ እንዳይዛት መንከባከቢያው እንደተዘጋ እንዲቆይ አዝዞናል። አሁንም ለበሽታ ልትጋለጥ ትችላለች። ደግሞ እኮ ገና የአንድ ሳምንት እንኳ እድሜ የላትም!

**48.** ትዕግስት: እንዴ፣ ምህረት፣ በሽተኞች ናችሁ እያልሽን ነው?

**49.** ምህረት: አይደለም ትዕግስት፣ እንደዚያ ማለቴ አይደለም…

***KW END***

**50.** ትዕግስት **(sniffles)**

**51.** አልማዝ: ለምንድን ነው የምታለቅሺው፣ ትዕግስት?

**52.** ትዕግስት: ምንም አይደለም…

**53.** ምህረት: ምን ነካሽ፣ ትዕግስት፣ ልትነግሪን ትችያለሽ!

**54.** ትዕግስት: እሺ…ከምኞቴ ጋር እያለሁ… **(sniffs)** …እኔም ያረገዝኩ መስሎኝ ነበር።

**55.** ምህረት/አልማዝ: ምን?

**56.** ትዕግስት: እናም ስለ ዶክተር ሮቤል ስትነግሪኝ፣ ምህረት…እንዲያየኝ ሄድኩ። እና ግን እንዳላረገዝኩ ነገረኝ። **(breaks down)**

**57.** አልማዝ: ግን ያ እኮ መልካም ዜና ነው! ለምን ታለቅሻለሽ ታዲያ?

**58.** ትዕግስት: **(cries)** ሁለት ጊዜ አስወርጄያለሁ፤ እናም ዶክተር ዘሪሁን በአግባቡ ስላልሰራልኝ ማህጸኔ ቆስሏል።ፈጽሞ ላረግዝ እንደማልችል ነግሮኛል። ከአሁን በኋላ ልጅ ሊኖረኝ አይችልም…

**59.** ምህረት: ወይኔ ትዕግስት! ምን ማለት እንደምችል አላውቅም!

**60.** አልማዝ: ነይ እዚህ ጋር!

**61.** ትዕግስት: **(sniffs)** አዝናለሁ…ደስታችሁን ማበላሸት አልፈልግም፣ ምህረት።

**62.** ምህረት: ትዕግስት፣ ባክሽን፣ ምንም አላደረግሽም!

**63.** ትዕግስት: **(pulling herself together)** ልጅሽ ታምራለች…ስም አውጥተሽላታል?

**64. SFX: SMS RECIEVED**

**65.** ምህረት: እስከ አሁን አላወጣሁላትም…

**66.** አልማዝ: ሄይ፣ መልእክት እየላከልሽ ያለው ማን ነው?

**67. SFX: BEEP AS SMS IS OPENED ON CELL PHONE**

**68.** ምህረት: እስኪ (reads) እንየዋ…(“ሃይ ምህረት፣ ሆስፒታል ውስጥ መሆንሽን ሰምቻለሁ። ደህና እንደሆንሽ ተስፋ አለኝ። ህጻኗም። ዳንኤል (deep breath)

**69.** ትዕግስት: ዋው!

**70.** አልማዝ: (surprised) ማን አሳሰበው…

**71.** ምህረት: (to herself) እንዲህ እንዲያደርግ ማን እንደነገረው አላውቅም…

**72. SFX: DOOR OPENS**

**73. SFX: FOOTSTEPS ENTER**

**74.** ንጉሴ: (shyly) ሃይ ምህረት…ዶክተሩ መግባት ይቻላል ብሎኝ ነው…

**75.** ምህረት/አልማዝ/ትዕግስት: (surprised) ንጉሴ!

**76.** ንጉሴ: ሃይ አልማዝ፤ ሃይ ትዕግስት፤

**77.** አልማዝ/ትዕግስት: ሃይ

**78.** አልማዝ: (to ትዕግስት) ትዕግስት፣ ለምን ውጪ አንቆይም?

(to ንጉሴ) ንጉሴ መቼም ነገ በትምህርት ቤት የዋና ውድድር ላይ የምናይህ ይመስለኛል፣ አይደለም?

**79.** ንጉሴ: አዎ እዛ እንገናኛለን!

**80. SFX: TWO PEOPLE LEAVE**

**81. SFX: DOOR CLOSES**

**82.** ንጉሴ: እንዴት ነሽ ምህረት?

**83.** ምህረት: በጣም ደህና ነኝ ንጉሴ። እዚህ ምን ትሰራለህ?

***KW BEGIN***

**84.** ንጉሴ: የሆነ ነገር አምጥቼልሻለሁ። ክፈቺው።

**85. SFX: PARCEL UNWRAPPED**

**86.** ምህረት: የህፃን አልባሳት! ዋው! አመሰግናለሁ! እንዴት ያምራሉ።

**(chuckles)** ምንአልባት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልኳ ይሆናል።

በጣም የምወደው ቸኮሌት! ወይኔ ንጉሴ፣ በጣም ደስ የምትል ነህ!

**87.** ንጉሴ: ለአንቺ ማንኛውንም ነገር ምህረት።

**88. SILENCE**

**89.** ምህረት: ንጉሴ?

**90.** ንጉሴ: ወዬ?

**91.** ምህረት: ይህን ሁሉ ነገር ለእኔ ለምን ታደርጋለህ? ስትጠይቀኝ እምቢ ብዬህ

የሌላ ሰው ልጅ ወልጄ፣ አሁንም እንደዚህ ትንከባከበኛለህ……

***KW END***

**92.** ንጉሴ: **(sighs)** ምህረት እኔ …እኔ አታውቂም። እስከ አሁንም

እወድሻለሁ።

**93.** ምህረት: **(cries)** ለእኔ በጣም ጥሩ ሰው ነህ፣ ንጉሴ…

**94. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 4: ንጉሴ WINS SWIMMING COMPETITION

**95. ATMO: SWIMMING POOL ATMO, PEOPLE TALKING**

**96. SFX: SWIMMING POOL**

**97. ትዕግስት:** ነይ፣ አልማዝ፣ እዚህ ጋር እንቀመጥ፤ መዋኛው ሙሉ ለሙሉ ይታየናል፡፡

**98. አልማዝ:** እሺ፣ ትዕግስት፡፡ ምህረት መምጣት ባለመቻሏ ያሳዝናል፡፡ ግን በዚህ ሰዓት የምታከናውናቸው ብዙ ነገሮች ይኖሯታል፡፡.

**99. COMMENTATOR: (over the loudspeaker)** ክቡራትና ክቡራን በዚህ የትምህርት ቤቶች የስፖርት ፌስቲቫል ላይ የሚሳተፉትን  የዋና ተወዳዳሪዎቻችንን በጥብጨባ ተቀበሏቸው!!

***KW BEGIN*** በመጀመሪያው ረድፍ ዮሴፍ አማረ ከኔልሰን ማንዴላ ትምህርት ቤት!

**100. HUGE CROWD: (applause)**

**101. COMM.:** በሁለተኛው መስመር ላይ፣ ፍቅረማርያም ከንቲባ ከኡቡንቱ ኮሌጅ!

**102. CROWD: (applause)**

**103. COMM.:** በሶስተኛው መስመር ላይ፣ ንጉሴ ጃለታ ከቦንጎ አካዳሚ!

**104. CROWD: (applause)**

**105. አልማዝ/ትዕግስት: (scream)** ን,,,,,ጉ ,,,,ሴ!

***KW END***

**106. COMM.:** ዋናተኞች፡- ተዘጋጁ…ተዘጋጁ…ጀምሩ!

**107. SFX: STARTING GUN**

**108. SFX: PEOPLE DIVE INTO THE POOL AND SWIM**

**109. አልማዝ/ትዕግስት:** **(scream)** በርታ ንጉሴ! በርታ ንጉሴ!

**110. COMM.:** ቀዘፋቸውን አጧጡፈዋልዋል! በመጀመሪያ አካባቢ ከፊት ከፊት ሲመራ የነበረው ከሁለተኛው መስመር ፍቅረማርያም ከንቲባ ቢሆንም ንጉሴ ጃለታ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተገልብጦ ተመልሷል!

**111. ትዕግስት/አልማዝ:** እንዲህ ነው! በርታ ንጉሴ!

**112. COMM.:** አሁን ንጉሴ ፍቅረማርያምን ቀድሞታል፣ ወደ መጨረሻው መስመር በመዝለቅ እየመራ ነው- ወደ ፊት እየተምዘገዘገ ነው- ንጉሴ ጃለታ አሸነፈ! ይገርማል! አሸናፊው ንጉሴ ጃለታ፤ እንዴት አይነት የሚደንቅ አጨራረስ ነው። ንጉሴ ጃለታ ከቦንጎ አካዳሚው አሸንፏል፥ **(FADE UNDER)**

**113. CROWD:** **(cheers)**

**114. አልማዝ/ትዕግስት** **(cheer more)**

**115. አልማዝ:** ዋው፣ ንጉሴ  ሰሞኑን ዋናው ላይ በጣም ማተኮር  ጀምሮ  እንደነበረ ነግሮኝ ነበር፡፡ ግን እንዲህ ችሎታ እንዳለው ታውቂ ነበር፣ ትዕግስት?

**116. ትዕግስት:** ኧረ ምንም አላውቅም፣ አልማዝ!

***KW BEGIN***

**117. COMM.:** አሁን ንጉሴ ጃለታን በከፍተኛ ሞራል ሲያበረታቱት ከነበሩት ደጋፊዎቹ አጠገብ ቆሜያለሁ። ። የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ርዕሰ መምህርት ሰብለም ከአጠገቤ ናቸው። ርዕሠ መምህርት ሰብለ ስለ ንጉሴ ብቃት ምን ተሰማዎት?

**118. JULIETTE:** **(excited, loudspeaker)** ንጉሴ ቦንጎ አካዳሚን አኮራ! በእዚህ ደረጃየትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር ላይ ተካፍለን ስናሸንፍ ይህ የመጀመሪያችን ነው! በጣም ተደስቻለሁ።.

***KW END***

**119. COMM.:** እዚህ ጋር ደግሞ አዲሱ አሸናፊ ንጉሴ ጃለታ ። እሺ ንጉሴ ምን ተሰማህ?

**120.** ንጉሴ: **(panting, loudspeaker)** ከዚህ ቀደም እንዲህ አይነት ደስታ ተሰምቶኝ አያውቅም! አስደናቂ ስሜት ነው!

**121. COMM.:** መቼም በአንፃራዊነት አዲስ ዋናተኛ ነህ፣ አይደለህም። ስለ አንተ ቀደም ሲል እንዴት አልሰማንም?

**122.** ንጉሴ: **(still panting)** እንግዲህ ዋና ጎበዝ እንደሆንኩ ያወቅኩት አሁን ነው።

**123. COMM.:** እንዴት አወቅኸው?

**124.** ንጉሴ: እውነቱን ለመናገር፤ በቅርቡ ትልቅ ችግር ውስጥ ገብቼ ነበር። እጽ መውሰድ፣ ጀምሬ ስለነበር ከእዛ የምወጣበትን መንገድ ከልብ ሳፈላልግ ነበር።። እድሜ ለየአቻ ለአቻ ምክክር እና ለቤተሰቦቼ እንዲሁም ለጓደኞቼ ድጋፍ የተሻለ ሱስ ውስጥ መግባት እንደምችል ስለተረዳሁ የበለጠውን ስፖርት በመስራት አገኘሁ!

**125. COMM.:** ስፖርት ከችግርህ ለመውጣት እንዴት ረዳህ?

**126.** ንጉሴ: በዋና አዳዲስ ጓደኞችን ማፍራት ስጀምር በራስ የመተማመን ስሜቴን መልሶ ገነባልኝ።

**127. COMM.:** ያንን አልፈህ የእዚህ አመት አዲሱ የትምህርት ቤቶች ውድድር አሸናፊ ለመሆን በቃህ! ንጉሴ ጃለታ ፣ አንዴ ሁላችሁም!

**128. CROWD: APPLAUSE**

**129. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

እዚህ ጋር ቢያንስ ለጊዜው ንጉሴን፣ አልማዝን፣ ትዕግስትን፣ ምህረትን፣ ዳንኤልን እና ሌሎችንም እንሰናበታለን። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ " በጀምስ ሙሐንዶ የተደረሰው «መዘዙን መቀበል" የተሰኘዉ ሁለተኛ ዙር ድራማ የመጨረሻ ክፍል ነበር። እዚህ ጋር መሰነባበቱን ካልፈቀዳችሁ ግን አልማዝ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዋን የምትቀርፅበትን የቪዲዮ ዘገባዋን ለመጨረሻ ጊዜ መመልከት ትችላላችሁ። በዘገባው አልማዝ መጨረሻ አካባቢ ላይ የተከሰቱት ነገሮች ምን አይነት ስሜት እንደፈጠሩባት ትናገረናለች። የቪዲዮ ዘገባውንም ሆነ የድራማውን ያለፉትን ክፍሎች ማድመጥ ወይንም ድራማዉን በአጠቃላይ በግል ማህደሮ ላይ መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረ-ገጽ አድራሻችን <u>dw.de/lbe</u> ላይ ያገኙታል። በፌስቡክ አድራሻችን ዝግጅቶቻችንን በመከታተል አስተያየታችሁን አኑሩልን። በሚቀጥለዉ ጊዜ እስክንገናኝ እዚህ ላይ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።